# ጥናት አንድ (ለዕብራዊያን መግቢያ)

የጥናት ዓላማ፡ በክርስትና ህይወት ቀን እየቆጠርን በሄድን ቁጥር ባለንበት እንድንረግጥ ሳይሆን እግዚአብሄር መንፈሳዊ እድገትን እንደሚጠብቅብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹በዚህ ጊዜ አስተማሪ ልትሆኑ ሲገባችሁ…ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ›› ዕብ 5፡11-6፡1

1. የዕብራዊያን መልዕክት ጸሃፊ ማነው?
2. የዕብራዊያንን መልዕክት አጀማመር ከሌሎች መልዕክቶች አጀማመር የሚለይት ምን ነገሮችን ትመለከታለህ?
3. ጸሃፊው የዕብራዊያን ሰዎች ዋነኛ ችግር አድርጎ የተመለከተው ነገር ምን እንደነበረ በአንድ አረፍተ ነገር በማጠቃለል ለመናገር ሞክር፡፡ ዕብ 5፡11-6፡3 ተመልከት
4. ይህ መልዕክት የሰዎቹን ችግር ለመፍታት የተጠቀመበት ዘይቤ ምን እንደነበረ በአንድ አረፍተ ነገር ማጠቃለል ቢያስፈልግ ምን ትላለህ?
5. ጸሃፊው መላዕክትን፣ ሙሴን፣ ኢያሱን፣ አሮንንና የብሉይ ኪዳንን አገልግሎት ሁሉ ሲጠቅስ ያንን ለማጣጣልና ለማናናቅ ነው ወይ? መልስህን አብራራ፡፡
6. 2፡2‹‹ስተን እንዳንወድቅ›› 3፡13‹‹ማንም በሃጥያት ተታሎ ልቡ እንዳይደነድን›› 5፡11‹‹ለመማር ዳተኛ ስለሆናችሁ›› 10፡29‹‹የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ›› 12፡25‹‹የሚናገረውን እርሱን እምቢ እንዳትሉት ተጠንቀቁ፡፡›› ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ ሰዎቹ ህይወት እድገት ወይም ማሽቆልቆል ምን ታያለህ? አስረዳ፡፡
7. 7፡27 9፡12፣26፣28 10፡10 እነዚህንና የመሳሰሉትን ክፍሎች ስናነብ ስለ ክርስቶስ መስዋዕት መረዳት የምንችለው አንድ ግልጽ እውነት ምንድነው?
8. ተራ ቁ3 ላይ እንደተጠቀሱት ሰዎች በጌታ ውስጥ የኖርክበት ጊዜና የደረስክበትን መንፈሳዊ ዕድገት ስትለካው ምን ይመስላል? በክርስትና ዕድሜ መቁጠር ብቻ ሳይሆን አድገን ሌሎችን የምናስተምርና የምንመክር እንድንሆን ጌታ ይጠብቅብናል፡፡

# ጥናት ሁለት ዕብራዊያን 1፡1-2፡4

የጥናት ዓላማ፡ በክርስቶስ በኩል የመጣው የፀጋ ወንጌል ሰዎችን ልቅና እንደፈለጉ በሃጥያት እንዲመላለሱ የሚያበረታታ ሳይሆን ይልቁኑ ከእነርሱ የተሻለ ቅድስና የተሞላው ህይወት እንደሚጠበቅባቸው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ለሰማነው ነገር አብልጠን ልንጠነቀቅ ይገባናን፡፡ ምክንያቱም በመላዕክት በኩል የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነና ማንኛውም መተላለፍና አለመታዘዝ ተገቢውን ቅጣት ከተቀበለ፤ እኛስ እንዲህ ያለውን መዳን ቸል ብንል እንዴት እናመልጣለን፡፡›› ዕብ 2፡1-3

1. ዕብ 1፡1-2፡4 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ላይ እግዚአብሄር የተናገራቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን ናቸው? እግዚአብሄር የተናገረባቸው ሁለት ዓይነት መንገዶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
2. በነዚሁ ቁጥሮች ላይ ‹‹በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ›› ሲል ጊዜውንና የተናገረባቸውን መንገዶች አስመልክቶ ምን ለማለት እንደፈለገ የምትረዳውን ሃሳብ ለወገኖች ግለጽ፡፡
3. በ1፡1-4 መሰረት፤ እግዚአብሄር የተናገረበት ሁለተኛው መንገድ ከመጀመሪያው መንገድ እንደሚበልጥ ወይም እንደሚሻል ጸሐፊው ያሰፈራቸው እውነቶች ምን ምንድናቸው?
4. ዕብ 1፡4-14 ያሉት ቁጥሮች ሊያስተላልፉ የፈለጉት ዋነኛው ሃሳብ ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
5. በቁ5 መሰረት ኢየሱስ ከመላዕክት የሚበልጥው በምን ምክንያት ነው? ቁ6-7 ያለው ክፍልስ ማወዳደሪያ ሃሳብ ያደረገውና የኢየሱስን ብልጫ ያሳየው በምን መንገድ ነው?
6. ቁ8-14 ያለው ክፍል ስለ መላዕክት የሚናገረው ሃሳብ ምንድነው? ስለ ኢየሱስስ ይህ ክፍል ምን ይናገራል?
7. ዕብ 2፡1 ላይ ለሰፈረው ማስጠንቀቂያ፤ በምዕራፍ አንድ ላይ ያነበብነው ክፍል ጥንካሬና ጉልበት ይሰጠዋል ብለህ የምታምነው በምን መንገድ ነው? አብልጦ መጠንቀቅ ሲል ምን ማለቱ ነው?
8. ዕብ 2፡1-4 ሲነበብ ይህ እኛ ያገኘነው ደህንነት ምን ዓይነት ደህንነት ነው ይላል? በክፍሉ መሰረት ይህንን ደህንነት ክቡር የሚያደርገው ምንድነው ይላል?
9. በዕብ 2፡1 ላይ ያለው ማስጠንቀቂያ እኛን በምን ዓይነት ሊመለከተን እንደሚችል አስረዳ፡፡ ሰዎችን በጸጋ ድናችኋል መመላለስ የሚኖርባችሁም በጸጋ ነው የሚለው ሃሳብ ሰዎችን ያባልጋቸዋል የሚለውን አመለካከት በዚህ ክፍል መነጽር ስትመዝነው ምን ያሳይሃል? የደህንነታችን መልዕክተኛና በእርሱ በኩል የመጣልን መልዕክት የከበረ ስለሆነ ደህንነታችንን በጥንቃቄ ልንይዘው ይገባናል፡፡

# ጥናት ሶስት ዕብራዊያን 2፡5-18

የጥናት ዓላማ፡ ዛሬ በዙሪያችንም ሆነ በውስጣችንን ከምናያቸው ነገሮች የተነሳ ለክብር የመብቃታችን ተስፋ የሚያጠራጥር ቢመስልም፤ ኢየሱስ የክብርና የምስጋና ዘውድ እንደጫነ በእምነት ማየት መቻላችን የእኛን ፍጻሜ በእርሱ ውስጥ መመልከት እንደምንችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ነገር ተገዝቶለት አናይም፡፡ ነገር ግን…ኢየሱስ የሞትን መከራ በመቀበሉ አሁን የክብርና የምስጋና ዘውድ ተጭኖለት እናየዋለን፡፡›› ዕብ 2፡8-9

1. ዕብ 2፡5-18 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ5 ‹‹ነገር ግን አንዱ በሌላ ሥፍራ…›› ይህ አንዱ የተባለው ጸሐፊ ማን ነው? ጥቅሱ የሚገኝበትን መጽሐፍና ከተቻለ ምዕራፉን ተናገር፡፡
2. ቁ6-8 ስለሰው ሁለት ዓይነት ገጽታዎች የሚያሳየን በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡
3. ቁ8ትን ስናነብ እግዚአብሄር ለሰው ልጅ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት ብሎ ይነግረናል፡፡ ለሰው ልጅ በአሁኑ ጊዜ ግን ሁሉም ነገር ተገዝቶለት አናይም፤ ይህ የሆነው ለምንድነው ትላለህ?
4. ኢየሱስን በቁ9 ላይ ስንመለከተው ከመላዕክት በጥቂት ስላነሰበት ምክንያት ምን ነበረ ይላል? በክፍሉ መሰረት ኢየሱስ በመሞቱ ያስገኘው ነገር ምንድነው?
5. በቁ8 እና በቁ9 መሃል ያለውን የሃሳብ ግንኙነት አስረዳ፡፡
6. በቁ10 ላይ የኢየሱስ መከራ መቀበል ምክንያት ሆኖ የቀረበው ሃሳብ ምንድነው? በዚህ ቁጥር ውስጥ ለኢየሱስ የተሰጠው ስም ምንድነው?
7. ቁ11-18 በእኛና በኢየሱስ ክርስቶስ መሃል ስላለው ግንኙነት ምን ይነግረናል? ኤፌ 2፡19፤ ኢየሱስ ሥጋን መልበስ ስለነበረበት ሌሎች ምክንያቶች ክፍሉ ምን ይናገራል?
8. ምዕራፍ አንድና ሁለት የኢየሱስን የተለያዩ ሁለት ገጽታዎችን ያሳዩናል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ምዕራፎች በተለያዩ መንገዶች የሚያሳዩንን ገጽታዎቹን ምንና ምን እንደሆኑ አስረዳ፡፡
9. ቁ10 እኛን ከክብር ለማብቃት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተ ይነግረናል፡፡ አሁን ካለንበት ሁኔታ ውስጥ ወጥተን ለተዘጋጀልን ክብር ለመብቃታችን በቁ8-9 ውስጥ ማረጋገጫ የሚሆንልህ ምን ሃሳብ ታያለህ? 1ኛዮሐ 3፡2፣ 2ኛ ቆሮ 4፡18 ስለእኛ ሞትን የቀመሰውና ወንድሞቼ ሊለን ያላፈረው ኢየሱስ ላጨልን ክብር ስለሚያደርሰን በእምነት እርሱን እያየን መመላለስህን ልትቀጥል ይገባሃል፡፡

# ጥናት አራት ዕብራዊያን 3፡1-6

የጥናት ዓላማ፡ የምንተማመንበትንና የምንመካበትን ክቡር ተስፋችን አጥብቀን መያዛችን፤ እውነተኛ የክርስቶስ ማደሪያዎች ማለትም ቤቱ መሆናችንን የሚያረጋግጥ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ክርስቶስ ግን በእግዚአብሄር ቤት ላይ እንደታማኝ ልጅ ነው፡፡ እኛም የምንተማመንበትንና የምንመካበትን ተስፋ አጥብቀን ብንይዝ ቤቱ ነን፡፡›› ዕብ 3፡6

1. ዕብ 3፡1-6 ያለው በአንድነት ይነበብ፡ ጸሃፊው ሰዎቹን የሚጠራባቸው ሶስት ስሞች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ‹‹ወንድሞች›› ሲል የማን ወንድሞች ማለቱ ነው?
2. በቅዱሳኑና በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ስላለው ግንኙነት ከቁ1 ላይ ምን ታያለህ? ጸሃፊው በዚህ ክፍል ውስጥ ‹‹ኢየሱስን አስቡ›› ሲል ምን ማቱ ነው? ለአንተ ኢየሱስን ማሰብ አስፈላጊ ሆኖ ታየዋለህ ወይ? ለምን?
3. በዚህ ምንባብ ውስጥ ሙሴና ኢየሱስ የሚመሳሰሉበት አንዱ ባህርይ ምንድነው? የሙሴ ታማኝነት የተመሰከረው በማነው? በቁ2 ላይ ቤት እየተባለ የሚነገርለትና ሙሴ ያገለገለበት የትኛው ቤት ነው? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ዘሁ 12፡4-8ትን ማንበብ ይረዳል፡፡
4. ቁ3 ላይ ቤትንና ቤትን የሚሰራውን ሲያወዳድር ሙሴን ያየው እንደ ምንድነው ማለት ነው? ኢየሱስንስ? በዚሁ ቁጥር ላይ የኢየሱስን ታማኝነት ይናገራል፡፡ ኢየሱሰ ታማኝነቱን ያስመሰከረባቸው መንገዶች የትኞቹ እንደሆኑ ተናገር?
5. ታማኝ የሚለውን ቃል እንዴት ትረዳዋለህ? የኢየሱስ ታማኝ መሆንና አለመሆን ከእኛ ጋራ ባለው ግንኙነት ረገድ ምን ለውጥ ያመጣል ትላለህ?
6. ቁ5 ‹‹ሙሴ ወደፊት ስለሚነገረው ነገር እየመሰከረ›› ይላል፡፡ ይህ ሙሴ ስለወደፊቱ የሚመሰክረው ነገር ምን ነበረ? ሉቃ 24፡27፣ ዮሐ 5፡46፣ ሥራ 26፡22-23፡፡ በሙሴና በኢየሱስ መካከል ስላለው ልዩነት ቁ5-6 ያለው ክፍል ያስተዋልካቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡
7. በቁ 6 ላይ የእግዚአብሄር ቤት በመባል የተጠቀሰው የትኛው ቤት ነው? ይህንን ቤትስ የሰራው ማን ነው?
8. በቁ6 መጨረሻ መሰረት እርሱ ታማኝ እንደሆነልን እኛም የምንተማመንበትንና የምንመካበትን ተስፋ አጥብቀን መያዛችን የሚያረጋግጠው አንድ እውነት ምንድነው? 3፡14ት ላይ ያለው ክፍል ይህንን ሃሳብ እንደሚያጠናክር ተናገር፡፡
9. አጥብቆ መያዝ ሲባል ምን ይገባሃል? አንተስ በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘኸውን ተስፋ ምን ያህል አጥብቀህና ተጠንቅቀህ ትይዘዋለህ? የያዝከው እምነትና ተስፋህ የቀልድ ስላልሆነ በጥንቃቄ አጥብቀህ ልትይዘው ትጋ፡፡

# <u>ጥናት አምስት ዕብራዊያን 3፡7-19</u>

የጥናት ዓላማ፡ የክርስትና ጉዞ በግሌ እወጣዋለሁ ብለን በተናጠል የምንሮጠው ህይወት ሳይሆን እርስ በእርሳችን በመደጋገፍ እየተበረታታንና እየተመካከርን በእምነት የምንጓዘው ጉዞ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነገር ግን በመካከላችሁ ማንም በሃጥያት ተታሎ ልቡ እንዳይደነድን ዛሬ እየተባለ ሳለ በየቀኑ እርስ በእርሳችሁ ተጽናኑ፡፡›› ዕብ 3፡13

1. ዕብ 3፡7-19 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጸሃፊው በቁ7-11 ላይ በጊዜው እየተናገረ ያለው ለማን ይመስልሃል? የሚናገረውስ ስለማን ነው?
2. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ የተሰጠው ዋነኛ ማስጠንቀቂያ ምን ነበረ? በእኛ ህይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ድምጹን የሚያሰማበትና እኛም ልባችንን ልናደነድን የምንችልባቸውን ሁኔታዎች ምሳሌዎችን በመስጠት አስረዳ፡፡
3. እግዚአብሄር በአባቶቻቸው ላይ የተቆጣሁበት ምክንያት ለምንድነው ይላል? ‹‹ተፈታተኑኝ›› ሲል ምን ማለቱ ነው? ታላላቅ ድንቅ ነገሮችን ጌታ በመካከላችን ቢሰራ ሰዎች ያምናሉ ወይም ይድናሉ ለሚለው አመለካከት ይህ ክፍል ምን ሃሳብ ይሰጣል?
4. ቁ9-11 ባለው ክፍል ውስጥ የእነዚህ ሰዎች ልብን ማደንደን የአንድ ጊዜ ስህተት ብቻ እንዳልሆነ የሚገልጽ ምን ሃሳብ ትመለከታለህ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የእግዚአብሄር ዕረፍት ሆኖ የተጠቀሰው ምንድነው?
5. ለዕብራዊያን ክርስትያኖች በቁ12 ላይ የተሰጣቸው ምክር ምን ነበረ? ቁ8፣ 10፣ 12፣ 13 … በነዚህ ቁጥሮች ሁሉ ላይ ትኩረት ተደርጎበት የምናየው አንድ ብልት ምንድነው?
6. በቁ16-19 የሚናገረው ስለ ስንት ዓይነት ሰዎች ነው? የእነዚህ ሰዎች ያለመግባታቸው ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው ነገር ምንድነው? እነዚህ ሰዎች አለማመናቸውን ያሳዩበትን በመጽሃፍ ቅዱስ የተነገረውን ሥፍራ ጠቁም፡፡
7. ዕብ 3፡7-19 ያለውን ክፍል በአንድ አረፍተ ነገር አጠቃለው ብትባል ምን ትላለህ?
8. ተመልሰህ ቁ13 ትን አንብብና ከልብ ድንዳኔ እንድንጠበቅ እግዚአብሄር መፍትሄ አድርጎ የሰጠው አንዱ ነገር ምንድነው ትላለህ? ይህንንስ ነገር እንድናደርግ የሚጠበቅብን ስንት ጊዜ ነው? ይህ መደረግ ያለበትስ መቼ ነው?
9. እርስ በእርስ የመጽናናትና የመበረታታትን ነገር ምን ያህል አስፈላጊ ሆኖ ታየዋለህ? ወገኖች ሊያቀኑህና ሊያስተካክሉህ ሲሉ ምን ያህል ፈቃደኛነት ታሳያለህ? ምሳ 27፡17ትን፣ 1ኛ ተሰ 5፡14 ይህ ጌታ ያዘዘልን መፍትሄና መድሃኒት ስለሆነ ልንጠቀምበት ያስፈልገናል፡፡

# ጥናት ስድስት ዕብራዊያን 4፡1-13

የጥናት ዓላማ፡ ምንም እንኳን ወከባና ጭንቅንቅ በሞላበት ዓለም ውስጥ ብንኖርም፤ እግዚአብሄር ለህዝቡ የተናገረው ዕረፍት ስላለ ወደተዘጋጀልን ዕረፍት ለመግባት በእምነት መትጋት እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ኢያሱ እረፍትን ሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ፤ ከዚያ በኋላ እግዚአብሄር ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር፡፡ ስለዚህ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሄር ህዝብ ገና ቀርቶለታል፡፡›› ዕብ 4፡8-9

1. ዕብ 4፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ የቁ1 ማስጠንቀቂያ ምንድነው? በአንተ አመለካከት ማስጠንቀቂያው የተሰጠው ለማን ነው ትላለህ?
2. በቁ2 ላይ እነዚያ የሚላቸው እነማን ናቸው? ይህ ለእነርሱ የተሰበከው ‹‹የምስራች ቃል›› የትኛው ቃል ነው? ለኛስ የተሰበከው የትኛው ነው?
3. በቁ2 መሰረት የእግዚአብሄር ቃል ጥቅም የማይኖረው ምንጊዜ ነው ይላል? በዚህ ክፍል መሰረት የማዋሃዱ ሃላፊነት የተጣለው በማን ላይ ነው? በአንተ ህይወትስ ቃሉ ሲጠቅምህ ታያለህ ወይ? ካልሆነስ ለምን?
4. የዚህ እረፍት ባለቤት ማን ነው? በቁ3 እና 6 መሰረት ወደዚህ እረፍት መግባት የሚከለክለው ነገር ምንድነው? ወደ እረፍቱ የመግቢያ ቁልፍ የሆነው ነገርስ ምንድነው?
5. ኢያሱ 21፡43-45 ስናነብ ተስፋ የተገባላቸው ሀገር ውስጥ እንደገቡና እረፍትንም እንደሰጣቸው እናያለን፡፡ ታዲያ በዕብ 4፡7-11 እንደገና የሚናገርለት እረፍት የትናው እረፍት ነው?
6. በቁ1 እና በቁ11 ድን በማቀናጀት በአንድ ዓረፍተ ነገር ጨምቀህ ተናገረው፡፡
7. በቁ12 ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ቃል የሚናገራቸውን ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር፡፡ ከነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት ሁሉ በላይ ለአንተ ህይወት የበለጠ ትርጉም የሚሰጥህ የትኛው ነው? ለምን ይህንን ለማለት እንደፈለክ አስረዳ፡፡
8. በቁ13 ላይ ስለ እግዚአብሄር ዓይን የተናገረው ነገር ወደ እረፍቱ ከመግባትና ካለመግባት ጋራ ምን የሚያገናኘው ነገር አለ?
9. መለስ ብለን ቁ8-10 ያለውን በማንበብ ይህንን እረፍት በሁለት በተለያዩ መንገዶች ልናይ የምንችልባቸውን መንገዶች አስረዳ፡፡ የአንተስ ህይወት በዚህች ምድር ላይ የእግዚአብሄርን እረፍት እየተለማመደች ነው ወይ? የዘላለሙስ እረፍት ምን ያህል ልብህን በተስፋ ይሞላዋል?

# ጥናት ሰባት ዕብራዊያን 4፡14-5፡10

የጥናት ዓላማ፡ እምነታችንን አጥብቀን ለመያዝ በምናደርገው ሙከራ መድካምና መውደቅ ሊኖር እንደሚችል፤ ነገር ግን ኢየሱስ የምናልፍበትን የሚረዳልን ብቻ ሳይሆን የሚራራልንም ሊቀ ካህናችን እንደሆነ በማወቅ በእርሱ ላይ ያለን እምነት እንዲዳብር ለመርዳት፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሄር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፣ እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ፡፡ በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤›› ዕብ 4፡14-15

1. ዕብ 4፡14-5፡10 በአንድነት ይነበብ፡፡ 4፡14-16 ባለው ክፍል ላይ የኢየሱስ ሹመት ምን ሆኖ ነው የምናየው? በክፍሉ ውስጥ የእርሱን ክህነት ታላቅ ያሰኙት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
2. በእነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ ለአንባቢዎቹ የተሰጡት ሁለት ትዕዛዞች ምንና ምንድናቸው? በአንተ አመለካከት፡ እምነትን አጥብቆ ለመያዝ ማበረታቻ ሆኖ የቀረበላቸው ሃሳብ ከዚህ ክፍል ውስጥ ምንድነው?
3. ቁ15 ‹‹ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤›› ይህንን ሲል ኢየሱስ እያንዳንዱን እኛ ያለፍንባቸው ነገሮች ሁሉ ውስጥ አለፏል ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ይመስልሃል? ማቴ 4፡1-10 ያለውንና 1ኛ ዮሐ 2፡16ትን በማነጻጸር ደግሞ የታየህን እውነት አካፍል፡፡
4. ቁ16ትን ትኩረት ሰጥተን ስናነብ መቅሰም የምንችላቸው ብዙ እውነቶች በውስጡ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ግልጽ የሆኑልህንና የታዩህን እውነቶች በመዘርዘር ተናገር፡፡
5. በ5፡1-4 ስለ ሊቀ ካህን ለመሆን የሚያስፈልጉትን ሶስት መስፈርቶች ተናገር፡፡ የሊቀ ካህን የሥራ ድርሻስ ምንድነው ይለናል? ሊቀ ካህን ርህራሄ ሊያሳይ ይችላል ተብሎ የሚታመንበት ምክንያት በዚህ ክፍል መሰረት ምንድነው ትላለህ?
6. ኢየሱስ እነዚህን በተራ ቁጥር 5 ላይ የተዘረዘሩትን የሊቀ ካህንነት መስፈርቶች የሚያሟላው በምን መንገድ እንደሆነ በዝርዝር አስረዳ፡፡ ዕብ 4፡15 ትንና 5፡3 ትን በማንበብ በአሮንና በኢየሱሰ መካከል የምታውን ጎልቶ የሚታየውን አንድ ልዩነት ተናገር፡፡
7. ቁ7-8 ትን የኢየሱስ ጸሎት ምን ነበረ? ጸሎቱ መልስ ስላገኘበት ምክንያት ክፍሉ ምን ይነግረናል?
8. በቁ7-9 ባሉት ክፍች ውስጥ መታዘዝ የሚለውን ሃሳብ ሶስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ከሶስቱ አኳያ እያንዳንዳቸው ምን ያስተምሩናል?
9. ይህ በቁ10 ላይ እግዚአብሄር የሾመልን ሊቀ ካህን፤ በዕብ 2፡፡18 ላይ ስናየው እኛን ለመርዳት ችሎታ ያለው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ዕብ 4፡15ት ስለዚህ ሊቀ ካህናችን የሚያሳየን ሌላ ገጽታ ምንድነው? እነዚህን ክፍሎች በማየት ልንደርስበት የምንችለው አንድ ማጠቃለያ ሃሳብ ምንድነው ትላለህ? ይህ ሃሳብ በህይወትህ እንዴት ሊጠቅምህ እንደሚችል ለወገኖች አካፍል፡፡

# ጥናት ስምንት ዕብራዊያን 5፡11-6፡3

የጥናት ዓላማ፡- ወንጌልን የሚያስተምሩን አስተማሪዎች ጠንከር ያለ ምግብና ወደ እድገት የሚያደርሰንን ትምህርት ማስተማር ይገባቸዋል ብለን እንደምንናገር ሁሉ፤ እኛም ሰሚዎቹ ወደ ፍጹምነት ሊያደርሰን የሚችለውን ህያው ቃሉን ለመስማት ዳተኞች መሆን እንደማይገባን ለማስጠንቀቅ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ ጉዳይ የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፤ ነገር ግን ለመማር ዳተኛ ስለሆናችሁ ለማስረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡›› ዕብ 5፡11

1. ዕብ 5፡11-6፡3 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ11 ላይ ‹‹ስለዚህ ነገር›› የተባለለት የትኛው ነገር ማለቱ ነው? በዚሁ ቁጥር መሰረት ስለዚህ ነገር መናገር ያልቻለበት ምክንያት ለምንድነው ይላል?
2. ጸሐፊው እነዚህን ሰዎች ሊገኙበት የሚገባቸው ሥፍራ የት ነበረ ይላል? እነርሱ አሁን ያሉበት ስፍራስ የት ነው ይላል?
3. በቁ12 ላይ ጸሐፊው በአሁኑ ጊዜ አስተማሪ አያስፈልጋችሁም ነበረ እያለ ነው ወይ ያለው? ካልሆነ ግን ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ፡፡
4. አንድ ሰው ቁ13ትን አንብቦ ‹‹ወተት የሚጠጣ ሁሉ ህጻን ነው›› ወደሚለው ሃሳብ ቢመጣ ትክክል ነው ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ ለወገኖች አስረዳ፡፡ 1ኛ ጴጥ 2፡2ትና ዕብ 5፡13ት ስለ ህጻንና ስለ ወተት የተናገሯቸውን ነገሮች አነጻጽር፡፡
5. በእነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ (11-14) በመንፈሳዊ ህይወት ያለመብሰል ምልክት ሆነው የምታያቸውን ቢያንስ አራት ነገሮችን ተናገር፡፡
6. ‹‹ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን›› ሲል በፊት ስለ ክርስቶስ የተማርነውን ነገር ትተን ሌላ ለብስለት የሚሆን ነገር እንማር ማለቱ ነው ወይ? አስረዳ፡፡ ዕብ 3፡14 በመጀመሪያ የነበረንን እምነት አጽንተን እንድንይዝ ከሚነግረን ሃሳብስ ጋር ይህ እንዴት ይሄድልናል?
7. በ6፡1-3 ውስጥ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ሆነው የሰፈሩት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ለምንድነው እነዚህን የተዘረዘሩትን ነገሮች ደጋግመን ማድረግ የማያስፈልገን?
8. ወደ ብስለት ለመሄድ ‹‹እግዚአብሄር ቢፈቅድ ይህን እናደርጋለን›› የተባለበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
9. ዛሬ ባጠናነው ክፍል መሰረት ጉድለት የምናየው ከአስተማሪው ነው ወይስ ከተማሪው? ጉድለት ሆኖ የሚታየው ነገር ምንድነው? ለእድገትህ ተገቢውን ምግብ አለማግኘትህ በአስተማሪው ላይ ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነ ከዛሬው ትምህርት ምን ያህል ተምረሃል? ቃሉን ለመስማት ስትቀርብ ዳተኝነት በውስጥህ እንዳይገኝ ሁልጊዜ ራስህን እየመረመርክ ወደ ቃሉ ቅረብ፡፡

# <u>ጥናት ዘጠኝ ዕብ 6፡4-20</u>

የጥናት ዓላማ፡- የተገባልን ተስፋ ጽኑና አስተማማኝ መሆኑን እግዚአብሄር በቃሉ ተናግሮ በተጨማሪ ደግሞ በመሃላው ያረጋገጠ ስለሆነ ነፍሳችን ያለሃሳብ ልታርፍ የምትችልበት መልህቅ እንዳለን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እግዚአብሄር የማይለወጥ ዓላማውን ለተስፋ ቃል ወራሾች ግልጽ ለማድረግ ስለፈለገ በመሃላው አጸናው…እኛም የነፍስ መልህቅ የሆነ ጽኑና አስተማማኝ ተስፋ አለን፤›› ዕብ 6፡17-19

1. ዕብ 6፡4-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ4-6 ላይ የምናነባቸው ሰዎች በህይወታቸው የተለማመዷቸውን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ በክፍሉ መሰረት ለምንድነው እነዚህን ሰዎች ወደ ንስሃ መመለስ የማይቻለው?
2. ቁ4-6 ላይና በቁ9-12 ላይ የሚናገራቸው ሰዎች አንድ ዓይነት ሰዎች ናቸው ወይስ የተለያዩ ናቸው? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አብራራ፡፡
3. ቁ7 ላይ የምናየት መሬት በቁ4-6 እና 9-12 ከሰፈሩት ሰዎች የትኛውን ትወክል ይመስልሃል? በቁ8 ላይ የምናየትስ የትኛውን ትወክላለች? መልስህን ሰፋ አድርገህ አስረዳ፡፡
4. ማቴ13፡5-6 ማቴ7፡21-23፣ ሥራ1፡17፣25 1ዮሐ2፡19 ትን በየተራ በማንበብ በቁ4-6 ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ ሊገናዘብ የሚችል ነገር ይኖራቸው አይኖራቸው መሆኑን በደንብ ተወያዩበት፡፡
5. በቁ9-11 ላይ ጸሐፊው ‹‹ከድነታችሁ ጋራ የተያያዘ ታላቅ ነገር›› የሚለው ነገር ምንድነው? ይህ የሚናገርለት ነገር በዳነ ሰው ህይወት ሁሉ ውስጥ መታየት ያለበት ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? እነዚህ ሰዎች እያደረጉ ስላሉት ነገር የተሰጣቸው ማበረታቻስ ምን ነበረ?
6. ቁ13-15 ባለው ክፍል በአብርሃም ህይወት ያለፈውን ነገር ማምጣት ያስፈለገበት ምክንያት ምንድነው ትላለህ?
7. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ቁ16-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ሊያረጋግጥ የፈለገው ዋና ሃሳብ ምንድነው? ማረጋገጫውንስ ለመስጠት የፈለገው ለማን ነበረ?
8. ቁ18 ‹‹እርሱ በሁለት በማይለወጡ ነገሮች በፊታችን ያለውን ተስፋ…እንድናገኝ አድርጓል፡፡›› እያለ የሚናገርላቸው እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
9. በአንተ አመለካከት የዘላለም ተስፋችንን ጽኑና አስተማማኝ የሚያደርገው ሃሳብ ምንድነው ትላለህ? በቁ12 መሰረት ተስፋውን አስመልክቶ ከእኛ የማይጠበቀውና በሌላ በኩል ደግሞ ከእኛ የሚጠበቀው ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ የተገባልህ የተስፋ ቃል አስተማማኝና ጽኑ ስለሆነ በእምነትና በትዕግሥት የተስፋ ቃሉን ለመውረስ ትጋትን አሳይ፡፡

# ጥናት አስር ዕብ 7፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- ከራሳችን ጸሎት ያለፈ፤ ስለ እኛ ዘወትር በአብ ፊት የሚጸልይልን ትጉህና ብቁ የሆነ ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ ስላለን፤ በእርሱ ላይ በእምነት በመደገፍ በድፈረት መኖር እንደሚቻል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ ስለእነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በህይወት ስለሚኖር፤ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሄር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡›› ዕብ 7፡25

1. ዕብ 7፡1-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ብቻ በመመስረት መልከ ጼዴቅ ማን ነው? በቁ1-2 ላይ በአብርሃምና በመልከ ጼዴቅ መካከል የተካሄዱትን ሁለት ነገሮች ተናገር፡፡
2. ቁ2-3 ላይ ስለ ስሙ ትርጉም ምን እንመለከታለን? አጠቃላይ ማንነቱን አስመልክቶ በእነዚህ ቁጥሮቸ ውስጥ የምናገኛቸውን ተጨማሪ መረጃዎች ዘርዝር፡፡
3. በተራ ቁጥር 2 ላይ የዘረዘርናቸው የመልከ ጼዴቅ ማንነቶች መልዕክቱ ለተጻፈላቸው ዕብራዊያን ሰዎች እንግዳ ሊሆኑ የሚችሉት በምን መንገድ ነው ብለህ ትገምታህ?
4. ቁ4 ሲጀምር የመልከ ጼዴቅን ታላቅነት በመናገር ነው፡፡ በቁ4-10 መሰረት መልከ ጼዴቅን ታላቅ ያሰኙት ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
5. ዕብ 6፡20ን በማንበብ መልከ ጼዴቅ የሚለው ሃሳብ የተነሳው የኢየሱስን ክህነት ለማስረዳት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ከዚህ አኳያ ስንመለከተው በ7፡1-3 የሰፈረው ሃሳብ ስለሊቀ ካህናችን ምን ያስተምረናል? 7፡4-10ስ ስለ ኢየሱስ የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?
6. ከክህነት ስርዓት ጋራ በተያያዘ ከቁ11-12 ውስጥ ልናወጣ የምንችላቸውን ቢያንስ ሶስት እውነቶች ተናገር፡፡ ቁ13-17 ክህነት ሊገኝ የሚችልባቸውን ሁለት መንገዶች ይጠቁመናል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ምንና ምንድናቸው?
7. ከ18-22 ያለው ምንባብ ከቀድሞው ክህነት አዲሱ ክህነት መሻሉን ለመሳየት የተናገራቸውን ሃሳቦች ዘርዝር፡፡ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሰፍሮ ያለ ካህን ስለሚያስፈልግበት ዋነኛ ምክንያት የሚናገር አንድ ሃሳብ አለ፡፡ ይህ በየትኛው ቁጥር ላይ እንደሚገኝና ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
8. ቁ23-24ትን በማንበብ እስከዛሬ ድረስ አሮን ብቻ ካህን ሆኖ ያልቆየበት ምክንያት ለምንድነው? በትውልድ ላይ የተመሰረተው ክህነትና በመልከ ጼዴቅ ባለው ክህነት መሃል ዋነኛ ልዩነት ሆኖ በከፍሉ የሰፈረው ነገር ምንድነው?
9. በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሄር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድን እንደሚችል የተጠቀሰው ምክንያት ምንድነው? ኢየሱስ ስለምንድነው እየማለደ ያለው ለሚለው ጥያቄ ሉቃ 22፡31፣ 1ኛ ዮሐ 2፡1 እና ከመሳሰሉት ክፍሎች ምን ሃሳብ ማግኘት እንችላለን? ኢየሱስ ያለማቋረጥ እየጸለየልህ መሆኑን ማወቅህ በውስጥህ ምን ስሜት ይፈጥራል? ድካምህን የሚረዳ፣ የጠላትን ሴራ የሚያውቅና፣ ጸሎቱ ሁልጊዜ የሚሰማለት ጌታ ስለሚማልድልህ በደስታና በምስጋና መንፈስ ተመላለስ፡፡

# ጥናት አስራ አንድ ዕብ 7፡26-8፡13

የጥናት ዓላማ፡- የቀድሞው ኪዳን በሰዎች ላይ ያለውን ጉድለት ማስወገድ የማይችል ስለሆነ እግዚአብሄር ጉድለትን ሊያስወግድ የሚችለውን በእርሱ ታማኝነት ላይ ብቻ የተመሰረተውን አዲስ የጸጋ ኪዳን እንደገባልን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የመጀመሪያው ኪዳን ምንም ጉድለት ባይገኝበት ኖሮ፤ ለሁለተኛው ሥፍራ ባልተፈለገም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሄር በህዝቡ ላይ ጉድለት በማግኘቱ…›› ዕብ 8፡7-8

1. ዕብ 7፡26-8፡13 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። ጸሐፊው በቁ26-27 ላይ ያስፈልገናል በማለት የሚናገረው ምን ዓይነት ሊቀ ካህናት ነው? ይህንን ስላለበት ምክንያት ከዚሁ ክፍል ምን ማየት እንችላለን?
2. በቁ28 መሰረት እግዚአብሄር ሊቀ ካህናትን የሾመባቸው ሁለቱ መንገዶች ምንና ምንድናቸው? በሁለቱ የሹመት መንገዶች መሃልስ የምንመለከተው ልዩነት ምንድነው?
3. በ8፡1-2 መሰረት የዕብራዊያን ጸሐፊ ላስተላልፍ የፈለግሁት ዋነኛ ነገር ምንድነው ይላል? በዚሁ ቁጥር ላይ ‹‹እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት…›› ሲል ሊያያይዝ የፈለገው ከየትኛው ሃሳብ ጋራ ነው?
4. ቁ6 ሶስት የተለያዩ ነገሮችን ያወዳድራል። እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እነዚህ የተሻሉ ሆነው የቀረቡት ሶስት ነገሮች ሁሉ የሚጠቁሙት ወደ ማን ነው ብለህ ታምናለህ?
5. ከቁ7-13 ያለውን ክፍል በማንበብ በተለይም ቁ7 የቀድሞው ህግ ጉድለት እንደተገኘበት መናገሩ ከእግዚአብሄር ጉድለት ያለበት ነገር ሊወጣ ይችላል ማለት ነው ወይ? አስረዳ።
6. ቁ9 ላይ የሚጠቀሱት በቃል ኪዳኑ ያልጸኑትና ቃል ክዳኑ የተገባላቸው አባቶች እነማን ናቸው? ዘጸ 19፡5-6፣ ዘጸ 24፡4-8ትን ስታይ የቀድሞው ኪዳን የተመሰረተው በምን ላይ ነበረ ትላለህ?
7. ቁ9 ‹‹በኪዳኔ አልጸኑም›› ‹‹እኔም ከእነርሱ ዘወር አልኩ›› እነዚህን ሁለት ሃሳቦች በመመርኮዝ እግዚአብሄር በዘጸዓት 19 እና 24 የገባውን ቃል ኪዳን ጡብቋል ብለህ ታምናለህ? አስረዳ። ዕብ 8፡10-12ትን ስታነብ አዲሱ ኪዳን የተገባው በማንና በማን መሃል ነው?
8. በዚያ ዘመን በነበሩ ሰዎችና በአሁን ዘመን ባለን ሰዎች መሃል የጉድለት መገኘትን አስመልክቶ ምን ልዩነት ያለን ይመስልሃል? አዲሱን ኪዳን ከቀድሞው የተሻለ የሚያደርገው ነገር ምንድነው? ቃል ኪዳኑ የተመሰረተው እንደ ቀድሞው ኪዳን በአንተና በእኔ ታማኝነት ላይ ስላልሆነ የተገባልንን ተስፋ ያለ ጥርጥር እንደሚፈጸም የሚያጠራጥር ነገር አይኖርም። ገላ 3፡18

# ጥናት አሥራ ሁለት ዕብ 9፡1-14

የጥናት ዓላማ፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እግዚአብሄር ወደሚገኝበት ወደ ውስጠኛው ክፍል ሰተት ብለን በመግባት መባና መስዋዕታችንን ማቅረብ የምንችልበት ድፍረት እንደተሰጠን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነገር ግን ወደ ውስጠኛው ክፍል የሚገባው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር፤ የሚገባውም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፤ ስለራሱ ሐጥያትና ህዝቡ ባለማወቅ ስላደረገው ሃጥያት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ ከቶ አይገባም ነበር፡፡›› ዕብ 9፡7

1. በቅድሚያ ዕብ 9፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-5 ላይ በመመርኮዝ በመቅደሱ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህ ነገሮች የሚገኙበት የመጀመሪያው ክፍል ማን ተብሎ ይጠራል?
2. ቅድስት ከተባለው ክፍል ቀጥሎ ያለው ክፍል ምን ተብሎ ይጠራል? ይህንን ክፍል ቅድስት ከተባለው ክፍል የሚለየው ነገር ምን ነበረ? በዚህ ክፍል የሚገኙት ሁለት ነገሮች ዘርዝር፡፡
3. የኪዳኑ ታቦት በውስጡ ምን ምንን ይዟል? መናው የሚገኘው ምን ውስጥ ነበረ? በታቦቱ ላይስ ስለነበረው ነገር ከዚህ ክፍል ምን እንመለከታለን?
4. እነዚህን አምስት ቁጥሮች ብቻ በማንበብና ጸሐፊው በቁ5 ላይ ነገሮቹን ዘርዝሮ ለመናገር አለመፍቀዱን ስትመለከት ስለ ቀድሞው ኪዳን ምን መናገር እንችላለን? በዚህ ካነበብንውና ጸሃፊው ከተናገረው አነጋገር በመመርኮዝ ሁለተኛው ኪዳን ይሻላል ለማለት እንዴት እንችላለን?
5. ቁ6-10ን አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ፡፡ በክፍሉ መሰረት በመጀመሪያው ክፍል ወይም በቅድስት ውስጥ የሚያገለግለው ማነው? ወደ ውስጠኛው ክፍል ስለሚገባው ሰውና ስለአገባቡ ሁኔታ ክፍሉ የሚናገረው ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
6. ቁ6--8 ላይ የምናነበው ነገር ሊያሳየን የሚችለው አንድ ትልቅ እውነት ምንድነው ትላለህ? መንፈስ ቅዱስ ከዚህ ሥርዓት እንድንማር የፈለገው ነገር በዚህ ክፍል መሰረት ምንድነው?
7. ‹‹አዲሱ ስርዓት እስኪመጣ›› ሲል ቁ9 የትኛውን ሥርዓት ማለቱ ነው? ለዚህ ሃሳብ ቁ11 መልስ ሊሆን የሚችለው በምን መንገድ ነው?
8. ቁ9ንና ቁ13-14 በማንበብ በብሉይ ኪዳን በሚቀርቡት መባና መስዋዕቶችና በአዲስ ኪዳኑ መስዋዕት መሃል የሚታየው ግለጽ ልዩነት ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡ ቁ9 ‹‹የሚያመልከውን ሰው ህሊና›› ቁ14 ‹‹እግዚአብሄርን እንድናመልክ›› የህሊና መንጻት እንዴት ነው ከአምልኮ ጋራ የሚያያዘው?
9. የመጀመሪያይቱን ድንኳንና(ቁ6-7) ሁለተኛይቱን ድንኳን(11-12) እያለ የሚናገራቸውን ሃሳቦች አነጻጽር፡፡ በተለይ በሁለተኛይቱ ድንኳን የሚከፍል መጋረጃ አለመኖሩና ሊቀ ካህናቱ ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መግባቱ ለራስህ ምን ያስተምርሃል? ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ የመግባት መብት ስለተሰጠህ ይህንን መብትህን በሚገባ ተጠቀምበት፡፡

# <u>ጥናት አስራ ሶስት ዕብ 9፡15-28</u>

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ካህናችን ሆኖ በአሁኑ ጊዜ በእግዚአብሄር ፊት መታየትና መማለድ ብቻ ሳይሆን የጀመረውን የደህንነት ስራም በማጠቃለል ለፍጹምነት የሚያበቃን እርሱ ራሱ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ሁለተኛም ጊዜ ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠባበቁት ድነትን ለማምጣት እንጂ ሃጥያትን ለመሸከም አይደለም፡፡›› ዕብ 9፡28

1. ዕብ 9፡15-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ15ትን ስናነብ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነበት ምክንያት ለምንድነው ይለናል? በዚህ ቁጥር ላይ የክርስቶስ ሞት የአዲስ ኪዳንን አማኞች ብቻ ሳይሆን የብሉይ ኪዳንንም ቅዱሳን እንደሚያድን የሚያሳየን ሃሳብ የትኛው ነው?
2. በቁ16-17ትን ስናነብ ጸሐፊው ስለኑዛዜ ምንነት ያስረዳል፡፡ ይህ ሃሳብ ከላይ ከተናገረው ሃሳብ ጋር በምን መንገድ ይያያዛል ብለህ እንደምታምን አስረዳ፡፡
3. ቁ20 ላይ ‹‹…እንድትጠብቁት እግዚአብሄር ያዘዛችሁ የኪዳኑ ደም ይህ ነው፡፡›› የመጀመሪያው ኪዳን እንዲጠብቁ የሚጠብቅባቸው ነገር እንዳለ እናያለን፡፡ ሁለተኛው ኪዳንም አዲስ ትዕዛዝ እንደተሰጠ በተለያየ ስፍራ ይታያል፡፡ ታዲያ ሁለቱም መጠበቅ ያለባቸው ነገር ካለ የሚለያቸው ነገር ምንድነው?
4. ቁ18-22 ያለው ይነበብና በተለይም በቁ18 ላይ ‹‹ስለዚህ የመጀመሪያው ኪዳን እንኳን ያለደም የጸና አልነበረም›› ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ዘጸ 24፡6-8 ቢነበብ የበለጠ ሃሳቡን ግልጽ ለማድረግ ይረዳል፡፡
5. በቁ24 ላይ በምድር የምትገኘውን መቅደስ ምን በማለት ነው የሚያስተዋውቃት? ክርስቶስ ወደ ሰማያዊቱ መቅደስ ስለገባበት ምክንያትስ ይህ ቁጥር ምን ይነግረናል? በዚሁ ቁጥር ላይ ‹‹ለመታየት›› ከሚለው አነጋገር ምን ትረዳለህ?
6. ሌሎች ካህናትንና ክርስቶስን በቁ25-26 ላይ ሲያነጻጽር ስለእነርሱ ‹‹በየዓመቱ…እንደሚገባ›› ሲል ስለእርሱ ደግሞ ‹‹ብዙ ጊዜ…አልገባም›› ይላል፡፡ ለምንድነው እርሱ ብዙ ጊዜ መግባት ያላስፈለገው?
7. በቁ27 ስለሰው ልጆች በተነገረውና በቁ28 ላይ ስለክርስቶስ የተነገረው መካከል የምታየው ዋነኛ ልዩነት ምንድነው?
8. በቁ28 መሰረት ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣው ለሚጠባበቁት ድነትን ለማምጣት እንደሆነ ይናገራል፡፡ እነዚህ ‹‹ለሚጠባበቁት የተባለላቸው ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ አምነው የዳኑ ሰዎች ናቸው ብለህ ታምናለህ? ከሆነስ ይህ የሚያመጣላቸው ድነት የትኛውን ድነት ነው?
9. ጌታችን ሲገለጥ የምትቀበለውን ፍጹም የሆነውን ደህንነት ምን ያህል ትጠማለህ? ዛሬ የስጋ ድካም፣ በሽታ፣ በመንፈስ መረበሽ፣ የስጋ ፈተና ማየልና የመሳሰለው ሁሉ ፍጹም ደኅንነት ሊሆን የማይችል የሩቅ ነገር አድርገው ቢያሳዩህም፤ ሊቀ ካህናችን ባላሰብነው ሰዓት ፍጹም ድነታችንን ይዞ ከች ስለሚል ተበረታታ!

# ጥናት አስራ አራት ዕብ 10፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሥራ በአብ ፊት ፍጹምነትን ያገኘን ሁላችን፤ እርሱ ያስገኘልንን ፍጹምነት በምድራዊ ህይወታችን ተግባራዊ ለማድረግ ከቅድስና ወደ ቅድስና የማደግ ፍላጎትና ጥረት እንደሚጠበቅብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ ይጠብቃል፤ ምክንያቱም በአንዱ መስዋዕት እነዚያን የሚቀደሱትን ለዘለዓለም ፍጹማን አድርጓቸዋል፡፡ ዕብ 10፡14

1. ዕብ 10፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1 ህጉን ምን በማለት ነው የሚያስተዋውቀን? ወደፊት የሚመጡ ያላቸውን ነገሮች በምን መንገድ ነው ያቀረባቸው?
2. በዚሁ ቁ1 ላይ መስዋዕቱ ማቆሚያ የሌለው ነገር እንደነበረ የሚጠቁሙን አራት የተለያዩ ቃላትን ተጠቅሟል፡፡ እነዚህ ቃላት ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ይህንኑ ቁጥር በመመርኮዝ በተደጋጋሚ ይቀርብ የነበረው መስዋዕት የህዝቡን ሃጥያት ማስወገድ ያልቻለው ለምንድነው?
3. ቁ1-4ትን ስታነብ የብሉይ ኪዳን መስዋዕት ህዝቡን ፍጹም ማድረግ ችሎ ቢሆን ኖሮ ይከሰቱ የነበሩት ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ ነው ጸሃፊው የሚነግረን?
4. መስዋዕቶቹ ሃጥያትን ካለማስወገድ አልፈው በሰዎች ህይወት ስለሚያስከትሉት ነገር በቁ3-4 ምን እናያለን? ማቴ 26፡27-28ትን በማንበብ አማኞች የክርስቶስን መስዋዕትነት ሲያስቡ ሊመጣላቸው የሚችለው ትዝታ ከዚህ በምን ይለያል? የጌታን ሞት ስታስብ ምን ይታሰብሃል?
5. ቁ5-8ትን አንብብና እግዚአብሄር አልፈለጋቸውምና ደስ አልተሰኘባቸውም የተባሉትን ነገሮች ተናገር፡፡ ለምንድነው እርሱ እነዚህን ነገሮች ያልፈለገውና ደስ ያልተሰኘባቸው?
6. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ክርስቶስ ስለመጣበት ምክንያት ምን ትመለከታለህ? በዓውደ ንባቡ መሰረት የእግዚአብሄር ፈቃድ ምን ነበረ ብለህ ታምናለህ?
7. ቁ10 ‹‹በዚህ ፈቃድ…ተቀድሰናል›› ይላል፡፡ ይህ ቁጥር ፈቃድ እያለ የሚናገረው ስለየትኛው ፈቃድ ነው? ከዚህ አነጋገሩ ስለቅድስናችን መነሻ/ምንጭ ምን መረዳት እንችላለን?
8. ዕብ 10፡11-12 ትን አንድ ሰው ረጋ ብሎ ያንብብ፡፡ ቁ11 ‹‹ካህን ሁሉ›› ቁ12 ‹‹ይኸኛው ካህን›› በመባል በሁለት የተከፈሉትን ክህነቶች አነጻጽር፡፡
9. ቁ14 ሲነበብ የቀደሙት መስዋዕቶች ሁሉ ያልፈጸሙት ይኸኛው መስዋዕት ያከናወነው አንድ ነገር ምንድነው? ቁ10 ‹‹ተቀድሰናል›› ቁ14 ‹‹ፍጹማን አድርጓቸዋል›› እያለ በሌላ በኩል ደግሞ ቁ14 ‹‹እነዚያ የሚቀደሱትን›› በማለት እንዳልተጨረሰ ነገር አድርጎ ማቅረቡ ለምንድነው ትላለህ?
10. ዕብ 10፡14 ፣ 12፡14 ፣ ፊሊ. 3፡12-15 ትንና እነዚህን የመሳሰሉ ክፍሎችን ስታነብ ቅድስናን አስመልክቶ ለራስህ ምን ትምህርት ታገኛለህ? ጌታን መቀበሌ እንጂ አረማመዴ አይጨንቀኝም ሚለውን አመለካከት ከእነዚህ ጥቅሶች አንጻር እንዴት ትመለከተዋለህ? ‹‹እነዚያ የሚቀደሱትን›› ከተባሉት መሃል ከሆንክ እርሱ የቀደሰውና ፍጹም ያረገው የሚቀደሱትን እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልግሃል፡፡ ለመቀደስ ተቀድሰናል ማለት ነው፡፡

# ጥናት አስራ አምስት ዕብ 10፡19-25

የጥናት ዓላማ፡- በመጨረሻው ዘመን ከመልካም ይልቅ ክፋት እንደሚገን፣ የብዙዎች ፍቅርም እንደሚቀዘቅዝ ጌታ ተናግሯል፡፡ ሆኖም ይህ በእኛ ህይወት እንዳይከሰት መፍትሄው እርስ በእርሳችን እየተገናኘን መበረታታትና መነቃቃት ሲሆን በተለይም ቀኑ መቅረቡን ስናይ አብዝተን ይህንን ማድረጋችን መፍትሄ እንደሚሆነን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ክፋት ስለሚገን የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል፡፡›› ማቴ 24፡12 ‹‹እርስ በእርሳችንም ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንዴት እንደምንነቃቃ እናስብ፡፡›› ዕብ 10፡22-24

1. ዕብ 10፡19-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ19 መሰረት እኛ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንድንገባ ያስቻለን ነገር ምንድነው? ወደዚህ ሥፍራ መግባት ትልቅ ነገር ሆኖ የሚነገርበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ? ጸሐፊው ድፍረት አግኝተናል ሲል ምን የሚያስፈራ ነገር ስላለ ነው?
2. በቁ 22 ያለው ክፍል እኛን አማኞችን ምን እንድናደርግ ይጠይቀናል? ጸሐፊው በድፍረት ይህንን እንዲል ያስቻለው ነገር ምንድነው? ይህ ክፍል ስንቀርብ በምን ሁኔታ እንድንቀርብ ነው የሚነግረን?
3. ቁ23 ላይ ሌላ እንድናደርግ የምንጠየቀው ነገር ምንድነው? ተስፋውን በተመለከተ አስቀድመን እንደወሰድናቸው የሚናገራቸው ሁለቱ እርምጃዎች ምንና ምንድናቸው? አጥብቀን መያዝ ስለሚኖርብን ምክንያት ክፍሉ ምን ይነግረናል?
4. በቁ24 ላይ ክርስትና በግል የምንኖረው ህይወት ብቻ እንዳልሆነ የሚጠቁሙንን ቃላቶች ሁሉ አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ ሥራ 20፡28 ኤፌ 4፡12 ትንና ዕብ 10፡24ትን በማንበብ መንጋን ስለመጠበቅ የምትረዳው እውነት ምን እንደሆነ ሰፋ በማድረግ ለማስረዳት ሞክር፡፡
5. በቁ 24-25 መሰረት፤ የእርስ በእርስ መነቃቃታችንና መበረታታችን ግቡ ምንድነው? በቁ24 ላይ ‹‹እንዴት እንደምንነቃቃ እናስብ፡፡›› ከሚለውን አነጋገር ምን መረዳት እንችላለን? ለዚህ መልስ ሆነው በቀረቡት ሃሳቦች ዙሪያ ራስህን ስትመዝን ከየት ታገኘዋለህ?
6. በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ልናደርግ ከተነገሩን መሃል የገባ እንዳናደርግ የታዘዝነው አንድ ነገር ምንድነው? በአንተ አመለካከት ሰዎች መሰብሰብን ሊተዉ የሚችሉባቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
7. በቁ25 ላይ ስብሰባ የሚለው በየእሁድ ጠዋት የሚደረገውን ነው ወይስ የትኛውን ስብሰባ ማለቱ ይመስልሃል? መልስህን አስረዳ፡፡ የስብሰባው አስፈላጊነት በይበልጥ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው መቼ ነው? ማቴ 24፡9-14ትን በማንበብ፤ በተለይም ቁ12 ከዚህ ክፍል ጋራ እንዴት ሊገናዘብ ይችላል?
8. ጌታ የሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል በመጨረሻው ዘመን በአማኞች መሃል ችግር ይሆናል ላለው ነገር በዛሬው ጥናታችን ውስጥ መፍትሄ አድርጎ የሚናገረን ነገር ምንድነው? በዘመኑ ፍጻሜ ሊመጣ ላለው መርዝ እግዚአብሄር መድሃኒት ብሎ የሰጠውን ይህንን መፍትሄ ምን ያህል ትጠቀምበታለህ? ለዚህ በሽታ መድሃኒት እንዳለው ላላወቁት ወገኖች ማሳወቅ የአንተም ሃላፊነት መሆኑን አትዘንጋ፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት ዕብ 10፡26-39

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ወደ እርሱ እንድንቀርብ በጸጋው የጋበዘንን ያህል፣ በዚያው መጠን ደግሞ ጸጋውን ያከፋፉትንና ሆን ብለው በሃጥያት ለመመላለስ በወሰኑ ሰዎች ላይ በአስፈሪ ቁጣና ፍርዱ እንደሚገለጥ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ሆን ብለን በሃጥያት ጸንተን ብንመላለስ…የሚቀረው ግን የሚያስፈራ ፍርድና የእግዚአብሄርን ጠላቶች የሚበላ ብርቱ እሳት መጠበቅ ብቻ ነው፡፡›› ዕብ 10፡26-27

1. ዕብ 10፡26-39 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ19-25 ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ ይህንን ክፍል ስታነጻጽረው የምትመለከተው ትልቅ ልዩነት ምንድው?
2. በዕብ 6፡4-6ና በዕብ 10፡26 ላይ የሚናገራቸው ሰዎች አንድ ዓይነት ናቸው ብለህ ታያለህ ወይ? መልስህን በመደገፍ ማብራሪያ ስጥ፡፡
3. ሆነ ብሎና በሃጥያት ጸንቶ የመመላለስን ሃሳብ በቁ29 ላይ ጸሃፊው የሰጠው ትርጉም ምንድነው? የሙሴን ህግ የናቀን ሰውና ሆን ብሎ በድፍረት በአዲስ ኪዳን በሃጥያት የሚመላለስን ሰው ይህ ክፍል የሚያነጻጽራቸው እንዴት ነው?
4. ቁ30 ላይ የምናነበው ‹‹ጌታ በህዝቡ ላይ ይፈርዳል›› የሚለው አነጋገር የተጻፈላቸውን ሰዎች አስመልክቶ የሚያጠናክርልን አንድ እውነት ምንድነው? ለምንድነው በቁ 30-31 ላይ የሚታየው እግዚአብሄር ብዙ ሰዎች እናውቀዋለን ከሚሉት እግዚአብሄር ጋራ የማይመሳሰልላቸው?
5. ጸሃፊው በቁ32-34 ላይ እነዚህን ሰዎች ወዴት እንዲመለከቱ ነው እየረዳቸው ያለው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሰዎቹ ቀድሞ ስለለፉበት ነገር የሚያስታውሳቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
6. ቁ34ት በአንድነት ይነበብ፡፡ እውቀት በአኗኗራችን ላይ ሊያስከትል ስለሚችለው አስተዋጽዖ ወይም ለውጥ ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ? አንተስ ስለምድራዊ ሃብትና ንብረት ያለህ አመለካከት ለሌሎች ለመራራት ሃብትህንም ለማካፈል የሚያበቃህ ዓይነት እውቀት ነው ወይ?
7. በቁ32-34 እነዚህ ሰዎች የኖሩት የህይወት ዓይነት በቁ35 ላይ ምን ብሎ ይጠራዋል? ጸሃፊው በዚህ ክፍል አንባቢዎቹን የሚያበረታታበት ሃሳብ ምንድነው?
8. ቁ36-39 ትን በማንበብ የጌታ ምጻት መቃረብ በእነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ ለሰፈረው ሃሳብ ማዕከላዊነት የሚኖረው ከምን አንጻር እንደሆነ ተናገር፡፡
9. በዕብ 10፡19-25 የታየው የፍቅር አምላክ ዛሬ ደግሞ በአስፈሪ ፈራጅነት መግለጡ ለእኛ ምን ትምህርት ይሰጠናል ትላለህ? ሆን ብሎ በድፍረት በሃጥያት ለመኖር መወሰንን እግዚአብሄር እንዴት እንደሚያየው ከዛሬው ትምህርት ተረድተን ጸጋውንና ቸርነቱን እያደነቅህ በምስጋና ልትመላለስ ይገባሃል፡፡

# ጥናት አስራ ሰባት ዕብ 11፡1-12

የጥናት ዓላማ፡- እምነት እግዚአብሄር የተናገረውን ወይም ደግሞ ተስፋ የገባውን ነገር የምንጨብጥበት መሳሪያ እንጂ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያስገኝልን መንፈሳዊ መሳሪያ እንዳልሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት…ነው›› ዕብ 11፡1 ‹‹የተስፋን ቃል የሰጠን ታማኝ ስለሆነ፣ አምነን የምንናገርለትን ተስፋ አጥብቀን እንያዝ፡፡›› ዕብ 10፡23

1. ዕብ 11፡1-12 በአንድነት ይነበብ፡፡ እምነት የሚያስፈልግባቸው ሁለት መስኮች በቁ 1 መሰረት ምንና ምንድናቸው? በእምነትና በተስፋ መሃል ስላለው ግንኙነት ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ?
2. በተራ ቁ1 ላይ የተመለከትናቸው የእምነት አገልግሎቶች፤ አንደኛው የሃላፊን ጊዜ፣ ሌላኛው ደግሞ የመጪን ጌዜ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁለት ሃሳቦች ለማስረዳት ሁለት ሁኔታዎችን ተጠቅመህ ምሳሌ በመስጠት ለወገኖች አስረዳ፡፡
3. በቁ 2 ላይ ‹‹አባቶች›› እያለ የሚጠራቸው እነማን ናቸው? ከአባቶች መካከል በቁ4 ላይ ለተጠቀሰው ለአቤል፤ እግዚአብሄር ምን በማለት ነበረ የመሰከረለት? በዚህ ቁጥር አነጋገር የአቤልን መስዋዕት ከቃየል የለየው አንድ ነገር ምን ነበረ?
4. ‹‹…ከመወሰዱም በፊት እግዚአብሄርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና፡፡›› ቁ5-6 መሰረት እግዚአብሄር በሄኖክ ደስ የተሰኘው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ሮሜ 14፡23 ትንና ዕብ 11፡6 በማየት እግዚአብሄር ለእምነት ስለሚሰጠው ሥፍራ ምን ትረዳለህ? የአንተ ህይወትስ ከዚህ አንጻር ምን ይመስላል?
5. ቁ7 ‹‹ኖህ ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሄር ባስጠነቀቀው ጌዜ…በእምነት ሠራ›› በቁ1 ላይ ካየናቸው ለእምነት ከተሰጡን ፍቺዎች የኖህ ሁኔታ የትኛውን ያንጸባርቅ ይመስልሃል? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ? ‹‹በእምነቱ ዓለምን ኮነነ›› ሲል ምን ትረዳለህ?
6. ቁ8-9 ውስጥ ስለ አብርሃም አወጣጥና ኑሮ የምታያቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡ አብርሃም ስለታዘዘበትና ስለኖረው አኗኗር ዓይነት ምክንያት ሆኖ የቀረበው ነገር ምን ነበረ? ‹‹እግዚአብሄር ለሚሹት ዋጋን እንደሚሰጥ ማመን አለበት›› የሚለው በቁ6 ላይ ያለው እውነት በአብርሃም ህይወት እንዴት ነው የተገለጠው?
7. ቁ11-12ትን ስታነብ አብርሃም የልጅ አባት ለመሆን ያበቃው ነገር ምን ነበረ? ይህ ክፍል የአብርሃምን እርጅና የሚገልጠው በምን መንገድ ነው?
8. በተራ ቁጥር 1 እና በተራ ቁ7 የምናየው እውነት ስለ እምነትና ተስፋ አለመነጣጠል ምን ያስተምረናል? እምነታችንን ልንመሰርትበት የምንችለው ተስፋ በመባል የምንናገረው ነገር የትኛውን ተስፋ ነው? ሁልጊዜ አለኝ የምንለው የተስፋ ቃል ታማኝ ከሆነውና ከማይዋሸው ከእግዚአብሄር የመጣ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት አስራ ስምንት ዕብ 11፡13-29

የጥናት ዓላማ፡- ይህች የምንኖርባት ዓለም ለእኛ ለጌታ ልጆች ቋሚ መኖሪያችን እንዳልሆነች፤ ነገር ግን መጻተኞችና እንግዶች መሆናችንን በመገንዘብ ከፊታችን ያለውን ተስፋችንን በእምነት እየተመለከትን መኖር እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እነዚህ ሁሉ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ሳያገኙ እምነታቸውን እንደጠበቁ ሞቱ፤ …በዚህ ምድር ሲኖሩ መጻተኞችና እንግዶች መሆናቸውን ተገንዝበው ነበርና።›› ዕብ 11፡13

1. ዕብ 11፡13-29 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። በቁ13 ላይ ‹‹እነዚህ ሁሉ›› በመባል የተጠቀሱት እነማን ናቸው? ይህ አነጋገር ሄኖክን፣ ኖህን፣ አቤልን አይጨምርም በሚለው ሃሳብ ትስማማለህ ወይ? አስረዳ።
2. ‹‹ከሩቅ አይተው ሰላም አሉት›› የሚለው በቁ13 ላይ ያለውን አነጋገር፤ በዮሐ 8፡56 ላይ ያለው ሃሳብ ምን ሃሳብ ይሰጠናል? በቁ13 ላይ የምናነባቸው ሰዎች ተገንዝበውት የነበረ ነገርና እኛ ደግሞ በዚህ ዘመን እንድንገነዘበው የተነገረን እውነት ምንድነው?
3. ቁ14-16ትን በማንበብ፡ እንደ መጻተኛና እንግዳ በዚህች ዓለም ላይ መኖራቸው የሚያረጋግጠው ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል ‹‹የመመለስ ዕድል ነበራቸው›› ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህንንስ በማለቱ ለእነዚህ ከእምነታቸው ለማፈግፈግ አዝማሚያ ለሚያሳዩ ሰዎች ምን መልዕክት ይሆናቸዋል ትላለህ?
4. ቁ13-16 ያለውን ክፍል በማንበብ እግዚአብሄር ለእነዚህ ሰዎች አምላካቸው ተብሎ መጠራት ያላፈረበት ዋነኛ ምክንያት በአንድ ዓረፍተነገር ተናገር።
5. በያዕ 1፡13ትና በዕብ 11፡17 የሚቃረን ሃሳብ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ። አብርሃምን በቁ17-19 ላይ ስትመለከት ታላቅ የእምነት ሰው ሊያሰኙት የሚችሉት ምን ነገሮችን ታያለህ?
6. በቁ20-22 የይስሃቅና የያዕቆብን ድርጊት እምነት የሚያሰኘው ምኑ ነው ብለህ ታምናለህ? የዮሴፍ ድርጊትስ የእምነት ድርጊት ተደርጎ ሊቆጠር የሚችለው በምን ምክንያት ነው?
7. ቁ24-29 ሙሴን አስመልክቶ በእምነት ያለፋቸውን ነገሮች ያሳያል። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሙሴ በእምነት የተከናወኑለትን ቢያንስ አራት ነገሮች ዘርዝር። በመጀመሪያውና በመጨረሻው የእምነት ክንውን መሃል ያሉት ስንት ዓመታት ይሆናሉ? ሙሴ እምነትን የተጠቀመው ፈርዖንን እንቢ ለማለት ብቻ ሳይሆን በገጠመኞቹ ሁሉ እንደሆነ እንመለከታለን፤ ከዚህ ለራሳችን ምን ትምህርት መውሰድ እንችላለን?
8. ካለህ እውቀት በመነሳት እንደ እንግዳ በመኖርና እንደ ባለቤት በመኖር መሃል ያሉትን ልዩነቶች ተወያዩባቸው። በእነዚህ ቁጥሮች መሰረት ሙሴ ህይወቱን የኖረው እንደ መጻተኛና እንግዳ ነበረ ሊያሰኝ የሚችለው ምንድነው?
9. የራስህን ህይወት ስትመለከት አኗኗርህ ወደ ባለቤት ወይስ ወደ እንግድነት ኑሮ ያጋድላል? ሰዎች ከዚህ አንጻር የአንተን ህይወት በተመለከተ የሰነዘሩት ሃሳብ አለ ካለ ችላ ሳትል ለማጤን ጊዜ ውሰድ። የእንግዳና የመጻተኛ ኑሮን ለመኖር ምን ነገሮች መቀየር እንደሚኖርብህ በሳምንቱ ውስጥ በማሰብ ለመለወጥ እንዲረዳህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ተወያይበት።

# ጥናት አስራ ዘጠኝ ዕብ 11፡29-40

የጥናት ዓላማ፦ የነአብርሃምንና የነዳዊትን ታላቅ እምነት በማየት እኔ ለትልቅ ቦታ አልበቃም እንዳንል፤ እንደ ጌዴዎን፣ ባርቅንና፣ ሳምሶንን የመሳሰሉትን ድክመታቸው ተገልጦ የሚታየውን ሰዎች የእምነት ጀግኖች አድርጎ የተጠቀመ እግዚአብሄርን እኛንም ማንነታችንን ተጠቅሞ ጠላቱን ማሳፈሪያ ሊያደርገን እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹እንግዲህ ከዚህ በላይ ምን ልበል? ስለ ጌዴዎን፣ ስለ ባርቅ፣ ስለ ሳምሶን፣ ስለ ዮፍታሄ፣ ስለ ዳዊት፣ ስለ ሳሙኤል፣ እንዲሁም ስለ ነብያት እንዳልተርክ ጊዜ የለኝም።›› ዕብ 11፡32

1. ዕብ 11፡29-40 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። ቁ29-30 ላይ እምነትን የሚለማመደው ማነው? በዚህ ቁጥር ላይ እስራኤላውያን እንዲሻገሩና ግብጻውያን ደግሞ ለመስጠማቸው ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
2. ቁ32 ላይ ‹‹እንዲሁም ስለ ነብያት እንዳልተርክ…›› ሲል በዚህ አባባሉ ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ሰዎችን በመጥቀስ ለምን የእምነት ሰዎች ልትላቸው እንደቻልክ አብራራ።
3. ቁ35 ‹‹ሌሎቹ ደግሞ…›› ይህ አነጋገር እምነታቸውን በሁለት ዓይነት መንገድ የተለማመዱ ሰዎችን ያሳየናል። እነዚህ ሁለቱ እምነታቸውን ስለተለማመዱበት መንገድ ምን ታያለህ? በቁ35 ላይ ስላሉት ሰዎች ከተነገረው ነገር የሚያስደንቅህ የትኛው ሃሳብ ነው? አንተስ እምነትህን በየትኛው መንገድ ነው እየተለማመድክ ያለኸው?
4. ቁ35 ላይ እግዚአብሄር ሁለት የእምነት ሰዎች ለገጠማቸው ተመሳሳይ ሁኔታ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ሲያስተናግድ እናየዋለን። ሰዎቹ የገቡበት ሁኔታ ምን እንደሆነና እግዚአብሄር ደግሞ ያስተናገደባቸውን ሁለት መንገዶች ሰፋ አድርገህ አስረዳ። ከዚህ ሁኔታ ስለ እግዚአብሄር አሰራር ምን ትማራለህ?
5. ዕብ 10፡32-39 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። በዚህ በተነበበው ክፍል መነጽር ስታየው ጸሐፊው በምዕራፍ 11 ላይ እነዚህ ሁሉ የእምነት ሰዎች ያለፉብትን መዘርዘሩ ለእነዚህ ሰዎች ሊያስተምር የፈለገው ማዕከላዊ ሃሳብ ምን ይመስልሃል?
6. በቁ39 ላይ ‹‹እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው…›› በማለት የሚናገረው ስለነማን ነው? መስካሪውስ ማነው ትላለህ? ለእምነታቸው የመመስከር ቦታ የአንተ ቢሆን በየትኛዎቹ ላይ ታተኩር ይመስልሃል? ከዚህ አንጻር በአንተና በእግዚአብሄር አመለካከት ምን ልዩነት ይታይሃል?
7. የእምነት ሰዎች ተብለው ከተጠቀሱት መሃል በተለይ በቁ32 ላይ ስላሉት ሶስት ሰዎች (ጌዴዎን፣ ባርቅና ሳምሶን) ህይወት የምታውቀውን ተናገር። ከአብርሃምና ከእነዚህ ሰዎች እኛ ላለንበት ህይወት የትኛው ይቀርባል? ለምን?
8. እግዚአብሄር እነዚህን ሰዎች የእምነት ሰው አድርጎ መጠቀሚያው ሊያደርጋቸው መቻሉ ምን ያስተምርሃል? በእግዚአብሄር እጅ ገብተህ ጠላቶቹን የሚያሳድድበትና የሚመታበት መሳሪያ ለመሆን ምን ያህል ተዘጋጅተሃል? የእግዚአብሄር መሳሪያ ለመሆን የሚጠይቀው ነገር ጥንካሬና ድፍረት ሳይሆን እምነትና እሺ ባይነት ነው።

# ጥናት ሃያ ዕብ 12፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- በከባድ ችግር ውስጥ በምናልፍባቸው ጊዜያት ውስጥ ምሳሌያችን ሊሆን የሚገባው ብኩርናውን ለምስር የሸጠው ዔሳው ሳይሆን፤ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን የታገሰው ኢየሱስ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።›› 1ኛ ቆሮ 10፡13 2ኛ ቆሮ 1፡8-11

1. ዕብ 12፡1-17 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። በቁ1 መሰረት ‹‹ምስክሮች›› የሚለው ቃል ሊተረጎም ይችላል የምትላቸውን ትርጓሜዎች ሁሉ ተናገር። የእነዚህ የእምነት አባቶች ያለፉበትና ምስክርነታቸው በምን መንገድ ነው ማበረታቻ ሊሆነን የሚችለው?
2. የቁ1ድን ሃሳብ ብትጨምቅና በአንድ ቃል ብቻ ግለጽ ብትባል ምን ትላለህ? በዚህ ክፍል ውስጥ ለሩጫ እንቅፋት ሆነው የተነገሩት ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ለድሉ ብቁ እንዲሆን አንድ ስፖርተኛ ሰው ማራገፍ ወይም መተው የሚኖርበት ምን ምን የመሳሰሉ ነገሮችን ነው? አንተስ ህይወት በፊትህ ላለው ሩጫ ሸክም ወይም እንቅፋት እየሆኑ የሚያደናቅፉህ ምን ነገሮች ታያለህ?
3. በቁ3 ላይ ከምታየው አነጋገር በእነዚህ አማኞች ህይወት እንዳይከሰት ወይም በመከሰት ላይ እንዳለ ጸሃፊው የፈራው ነገር ምን ታያለህ? ወደዚህ ወዳሉበት ሁኔታ ሊያመጣቸው ያለው ነገር ምንድነው? ወደዚህ ሁኔታ እንዳይገቡ መፍትሄ ይሆናቸዋል የሚለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
4. ቁ3-11ድን ትኩረት ሰጥተህ በማንበብ ይህ እያለፉ ላሉበት ሁኔታ ተጠያቂው ማነው ትላለህ? በዚህ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሄር ሃላፊነት ምንድነው?
5. በቁ9-10 ላይ በምድራዊ አባቶቻችንና በሰማያዊ አባታችን መሃል የታዩትን ማነጻጸሪያ ሃሳቦች ተናገር። በቁ11 ላይ ‹‹በወቅቱ›› እና ‹‹በኋላ ግን›› የሚሉት ቃላት ስለ ቅጣትና ውጤቱ ምን ይነግሩናል?
6. ወረድ ብለን ቁ16 ላይ ለምንድነው ዔሳው ‹‹በወቅቱ›› እና ‹‹በኋላ ግን›› ለሚለው ሃሳብ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው?
7. እንደገና ቁ9-10ርን በማንበብ እግዚአብሄር ልጆቹን በቅጣት ውስጥ በማሳለፍ በውስጣቸው እየሰራ ያለው ምን ዓይነት ባህርዮችን ታያለህ? በቁ14 ላይ እንድናደርግና እንድንፈልግ የታዘዝናቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
8. በቁ9-10 እንዳየነው እግዚአብሄር በልጆቹ ህይወት እየሰራ ያለውንና፤ በቁ14 ደግሞ ልጆቹ እንዲያደርጉት ያዘዘው ሁለት ነገሮችን አነጻጽር። እግዚአብሄር በህይወታችን እየሰራ ያለውን ነገር እንድንሰራ መጠየቃችን ምን ያስተምርሃል?
9. በቁ16 ስለ ዔሳውና በቁ2 ላይ ደግሞ ስለ ኢየሱስ የተነገሩትን ሃሳቦች በማነጻጸር ተናገር። ሰዎች እንደ ዔሳው በጊዜያዊ ችግራቸው የሚበለጠውንና የሚሻለውን ለመጣል የሚወስኑት ለምን ይመስልሃል? አንተስ ከምታልፍበት ሁኔታ ክብደት የተነሳ የመጣው ይምጣ ብለህ ልትጥል ያለኸው መልካም ነገር አለ ወይ? አይዞህ! በቁ2 ላይ የጌዜውን ታግሶ የዘላለሙን ለማየት ተስፋ እንዲሆንህ ኢየሱስን በመመልከት ሩጫህን ሩጥ።

# <u>ጥናት ሃያ አንድ ዕብ 12፡18-29</u>

የጥናት ዓላማ፡- ኑሯችንና ህይወታችን ሁሉ አምልኮ ነው ብለን የምናምን ከሆነ፤ እግዚአብሄር ሊመለክ የሚፈልግበትንና ደስ የሚያሰኘው ነገር ምን እንደሆነ እንድናውቅ ሁልጊዜ መማርና መመርመር እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በቀረውስ ወንድሞች ሆይ እግዚአብሄርን ደስ ለማሰኘት እንዴት መኖር እንደሚገባችሁ አስተምረናችኋል…ስለሆነም በጌታ በኢየሱስ የምንለምናችሁና የምንመክራችሁ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ በዚሁ እንድትገፉበት ነው፡፡›› 1ኛ ተሰ 4፡1

1. ዕብ 12፡18-29 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ18-21ትና በቁ22-24 ላይ የምታያቸው ሰዎች በስሜታቸው ምን ልዩነት ታያለህ? በቁ22-24 ባለው ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩትን ስሞች ሁሉ አንድ በአንድ ተናገር፡፡
2. የአቤል ደም እንደሚናገር ቁ24 ይነግረናል፡፡ የአቤል ደም የሚናገረው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? የኢየሱስ ደም ደግሞ የሚናገር እንደሆነና ከአቤል የተሻለ ቃል እንደሚናገር እናነባለን፡፡ የኢየሱስ ደምስ የሚናገረው ቃል ምንድነው? ለምን ከአቤል የተሻለ ቃል ይናገራል እንደተባለለት አስረዳ፡፡
3. በቁ25 ላይ ‹‹የሚናገረውን እርሱን እንቢ እንዳትሉት ተጠንቀቁ፡፡›› ሲል ተናጋሪው ማነው? ዕብ 2፡1-3 ያለው ክፍል በዚህ ቁጥር ከምናየው ጋራ በማገናዘብ የምትረዳውን ተናገር፡፡
4. በቁ26-28 ውስጥ ተደጋግሞ የተነገረ ቃል ምንድነው? ይህ ቃል በእነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ ስንት ጊዜ ተጠቅሷል? ይህንን ቃል በዚህ ሥፍራ ላይ በመጠቀም ሊያስተላልፍልን የፈለገው መልዕክት ምንድነው ትላለህ?
5. የማይናወጥ መንግሥት የመቀበላችን እውነት በውስጣችን ሊፈጥር ስለሚገባው ስሜት የዛሬው ምንባብ ምን ይነግረናል? ይህንን የመሰለ መንግሥት መቀበላችን፤ ከምሥጋና ሌላ ምን ማስከተል ይኖርበታል?
6. ዕብ 10፡19 ንና 1ኛ ዮሐ 5፡14 የመሳሰሉትን ክፍሎች ስንመለከት ወደ እግዚአብሄር በድፍረት መቅረብና ያስተምሩናል፤ ይህ ቁ28 ደግሞ በፍርሃት መቅረብንና ማምለክን ይነግረናል፡፡ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ የሚመስሉ ሃሳቦች እንዴት እንደምትረዳቸው ተናገር፡፡
7. በቁ28 ላይ እግዚአብሄርን እንድናመልክ የተጠየቅንባቸው ሶስቱ መንገዶች ምን ምንድናቸው? ሮሜ 14፡15-18 ሲነበብ እግዚአብሄርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ማምለክ ወይም ማገልገል የሚለው ሃሳብ በሥራ ሲገለጥ በዚህ ክፍል መሰረት ምን ማለት እንደሆነ ተናገር፡፡
8. 1ኛ ተሰ 4፡1 ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎችን ያስተማረው የትምህርት ዓይነት ምን ነበረ? እነዚህ ምዕመናን የተማሩት ትምህርት በዕብ 12፡28 መነጽር ስትመለከተው ለህይወታቸው እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው በምን መንገድ ነው?
9. ስለ እግዚአብሄር ማንነት በማወቅና በአምልኮ መሃል ያለውን ግንኙነት አስበኸው ታውቃለህ ወይ? ደስ የሚያሰኘውን ካላወቅን ተቀባይነት ያለው ዓይነት አምልኮ ማቅረብ እንደማንችል ከዚህ እንረዳላን፡፡ ጳውሎስ ‹‹አስተምረናችኋል›› እንዳለው አንተም የአምልኮ ህይወትህ እግዚአብሄር የሚቀበለው እንዲሆን ደስ የሚያሰኘው ነገር ምን እንደሆነ ከቃሉ ለራስህ የማወቅና ወገኖችህ ደግሞ እንዲያውቁ የመርዳት ሃላፊነትህን አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሃያ ሁለት ዕብ 13፡1-8)

የጥናት ዓላማ፡- እኛ ሁላችን የእግዚአብሄርን ቃል የነገሩን ሰዎች የኑሯቸው ፍሬ በመሆናችንና፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ትናንት፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ስለሆነ፤ በእኛም ኑሮ የሰዎችን ህይወት ሊለውጥ እንደሚችል በማመን የእነርሱን ፈለግ በመከተል ወንጌልን መናገር እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የእግዚአብሄርን ቃል የነገሯችሁን መሪዎቻችሁን አስቡ፤ የኑሯቸውን ፍሬ ተመልከቱ፤ በእምነታቸውም ምሰሏቸው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው፡፡›› ዕብ 13፡7-8

1. ዕብ 13፡1-8 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-6 ውስጥ አማኞች ቢያንስ ከስድስት ዓይነት ሰዎች ጋራ ሊኖራቸው ስለሚገባው የግንኙነት ዓይነቶች  እንመለከታለን፡፡ እነዚህን ስድስቱን አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ እነዚህን የዘረዘርካቸውን ስታይ ከላይ ወደታች ተዋረዱን ስታይ ምን ትገነዘባለህ?
2. በቁ1-3 ውስጥ እንድናስባቸው የታዘዝናቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ሁለቱንም እንድናስባቸው በተነገረን አነጋገር ላይ ምን የሚመሳሰል ነገር ታያለህ? በመከራ ውስጥ ለሚያልፉ ለወገኖች ስትጸልይ ወይም ማናቸውንም ነገር ስታደርግ ምን ያህል እንደራስህ አድርገህ እየተሰማህ ታደርገዋለህ?
3. በቁ4 ላይ ጋብቻን አስመልክቶ የሰጣቸው ሁለት ትዕዛዞች ምንና ምንድናቸው? እነዚህን ትዕዛዛት ላለመጠበቅ ወይም ላለመከተል በወሰነ ሰው ላይ እግዚአብሄር ስለሚወስደው እርምጃ ከክፍሉ ምን እንማራለን? በዚህ ክፍል ካነበብነው ነገር ስታይ እግዚአብሄር ስለ ትዳር ስላለው አመለካከት ምን ትረዳለህ?
4. በዕብ 13፡5 እና በፊሊ. 4፡12-13 ባሉት ክፍሎች መሃል ስላለው ተመሳሳይነት የምታየውን አስረዳ፡፡
5. ቁ6 ላይ ‹‹ስለዚህ በሙሉ ልብ›› የሚለው አነጋገር፤ ይህ ሰው ሊያደርግ ወይም ሊሰራ ላሰበው ነገር ሙሉ ልብ ያገኘው ከምንድነው ማለት እንችላለን?
6. በቁ7 ላይ እንድናደጋቸው የተሰጡን ሶስት መመሪያዎች ምን ምንድናቸው? በቁ3 ላይ የተመለከትነው አስቧቸው የሚለው ቃልና በቁ7 ላይ ያለው አስቧቸው የሚለው ቃል አጠቃቀም ላይ ምን ልዩነት እንደምታይ ተናገር፡፡
7. እነዚህ በቁ7 ላይ ያየናቸው ሰዎች የኑሯቸው ፍሬ እንድመለከት የተነገረን ፍሬያቸው ምንድነው?
8. ‹‹በእምነታቸውም ምሰሉአቸው፡፡›› በዚህ ክፍል እነዚህ የእግዚአብሄርን ቃል የነገሩን ሰዎች አምነዋል የሚያሰኛቸው ይህ ነገር ምን ነበረ? እኛንስ ‹‹በእምነታቸው ምሰሏቸው›› ሲለን ምን ማለቱ ነው? ከዚህስ አንጻር የኢየሱስ ክርስቶስ አለመለወጥ ምን ግንኙነት ይኖረዋል ትላለህ?
9. በአንተ ውስጥ በእምነት የወንጌልን ቃል የዘሩት ሰዎች ፍሬ መሆንህን ምን ያህል ትገነዘበዋለህ? እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች አዘውትሮ ማሰብ ወንጌልን ለመመስከር እምነት በውስጥህ እንዲያድግ ለማድረግ ስለሚረዳህ  ቃሉ እንደሚናገር በእምነታቸው ልትመስላቸው ትጋ፡፡

# ጥናት ሃያ ሶስት ዕብ 13፡9-16

የጥናት ዓላማ፡- እርሱ አምላክነቱን ትቶ እኛን ለመቀደስ ከሰፈር ውጭ ውርደትንና ነቀፋን እንደተቀበለ፤ እኛም ሌሎችን ወደ ህይወት እናምጣ ካልን ካለንበት ከተመቻቸና ከሞቀ ሁኔታ ውስጥ መውጣትና እርሱ ባለፈበት ነገሮች ሁሉ ውስጥ ለማለፍ ፈቃደኞች መሆን እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ እኛም እርሱ የተሸከመውን ውርደት ተሸክመን ከሰፈር ውጭ ወደ እርሱ እንውጣ፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቋሚ ከተማ የለንም፤ ነገር ግን ወደፊት የምትመጣዋን ከተማ እንጠብቃለን፡፡›› ዕብ 13፡13-14

1. ዕብ 13፡9-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጸሐፊው በ13፡9 ላይ የዕብራዊያንን ሰዎች የሚመክረው ምን በማለት ነው? ስለልብ ጽናትስ ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ?
2. በቁ10 ላይ ‹‹በድንኳኒቱም የሚያገለግሉ ከዚያ ሊበሉ መብት ያላገኙበት መሰዊያ አለን፡፡›› ሲል 1ኛ ቆሮ 9፡13 እና 10፡18 ካለው ሃሳብ ጋራ በማገናዘብ ምን ማለቱ ይመስልሃል?
3. ሐዋ ሥራ 7፡58 ዘኁ 15፡32-36 ዘሌ 24፡21-23 ንና የመሳሰሉትን ክፍሎች ስትመለከት ይህ ‹‹ከከተማው በር ውጭ›› ወይም ‹‹ከሰፈር ውጭ›› የሚለው ሃሳብ ምን ትርጉም ይሰጥሃል? የኢየሱስ ከከተማ በር ውጭ መከራን መቀበል በዚህ ሃሳብ መሰረት ምን ማለት እንደሆነ ነው የሚገባህ?
4. ኢየሱስ ከከተማ በር ውጭ መከራን ስለተቀበለበት ምክንያት ምን እንረዳለን? በቁ11-14 ባለው ክፍል ውስጥ እነዚህ በክርስቶስ ደም የተቀደሱት ሰዎች የቀደሳቸውን ኢየሱስን እንዲመስሉ የተጠየቁት አንድ ነገር ምንድነው?
5. ዕብ 13፡15 ትንና 1ኛ ተሰ 5፡17 ትን በአንድ ላይ አድርገን ብናስቀምጥ ምስጋናን አስመልክቶ ከእነዚህ ሁለት ክፍሎች ለህይወታችን ምን መመሪያን ማውጣት እንችላለን? በቁ15 ላይ ምስጋና ምን ተብሎ ነው የተጠራው?
6. በዕብ 13፡15-16 ውስጥ ስንት ዓይነት መስዋዕቶችን ትመለከታለህ? ዘርዝራቸው፡፡ በዚህ ክፍል መስዋዕቶቹ የተሰጣቸው ልዩ መለያ ምንድነው ማለት እንችላለን?
7. ዘጳ 23፡12፣ ዘሁ 31፡19፣ ዘሌ 14፡3፣ ዘሌ 24፡13-14 ትንና የመሳሰሉትን ክፍሎች በማንበብ ‹‹ከሰፈር ውጭ›› የሚገኙትን ነገሮች ዘርዝር፡፡ በሰፈር ውስጥና በሰፈር ውጭ ምን ልዩነት ሊኖር ይችላል ትላለህ?
8. በእኛ ዘመን ‹‹ሰፈር ውስጥ›› የሚለውን ትርጉም እንዴት ልንወስደው እንችላለን? ኢየሱስ ወዳለበት እንድንወጣ ስንጠየቅ፤ ‹‹ከሰፈር ውጭ›› ለሚለው ቃል ካለህ መረዳት ጋራ ለእኛ ምን ማለቱ ነው? የዚህ ዓይነቱን መስዋዕትነት ለመክፈል ልብህ ምን ያህል ዝግጁ እንደሆነ ራስህን መርምር፡፡

# ጥናት ሃያ አራት ዕብ 13፡17-25

የጥናት ዓላማ፡- አማኞችን ‹‹አገልጋይና ተራ ምዕመን›› ‹‹አገልጋይና ተገልጋይ›› በማለት የምንከፋፍልበት አነጋገር የተሳሳተ አመለካከት እንደሆነና፤ መከፈል ካስፈለገን ‹‹መሪዎች›› እና ‹‹ቅዱሳን›› የሚለው መጽሃፍ ቅዱሳዊ መሰረት እንዳለው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ለመሪዎቻችሁ ሁሉና ለቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡›› ዕብ 13፡24

1. ዕብ 13፡17-25 ያለው በህብረት ይነበብ፡፡ በቁጥር 17 ላይ የምንታዘዘው ምን እንድናደርግ ነው? ለዚህ ምክንያት ሆኖ የተነገረን ነገርስ ምንድነው?
2. ለመሪዎቻችን አለመታዘዛችንና አለመገዛታችን ሊያስከትል የሚችላቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት የመሪዎቻችን ዋነኛ ሃላፊነት ሆኖ የቀረበው ነገር ምንድነው?
3. ‹‹መሪዎቻችሁ›› ‹‹ተገዙላቸው›› ‹‹ይተጋሉ›› የሚሉት ቃላት ስለ ቤተክርስትያን መሪ የሚጠቁመን አንድ ዋነኛ እውነት ምንድነው ትላለህ? በቁ 17 መሰረት ከመሪ የሚጠበቀው ምንድነው? ከምዕመናንስ?
4. በቁ18 ላይ ጸሃፊው ከአንባቢዎች የሚጠይቀው አንድ ነገር ምንድነው? ሮሜ 1፡12ትንና ይህንን የጸሎት ጥያቄ በማገናዘብ አገልጋይ ስለሚያገለግላቸው ሰዎች ሊኖረው ስለሚገባው አመለካከት ምን ትማራለህ?
5. በቁ20-21 ላይ በአንባቢዎቹ ህይወት እንዲፈጸም የሚሻቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህ ሁለት ነገሮች በምን መንገድ ነው የሚደጋገፉት?
6. ‹‹ለእርሱ እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን›› የሚለው ከላይ ከተነገረው ሃሳብ ጋራ እንዴት ሊያያዝ ይችላል ብለህ ታምናለህ?
7. ቁ23-25ትን ስናነብ የጢሞቲዎስ በዚህ ቦታ መጠቀስ ስለ ዕብራዊያን ጸሃፊ ምን ይጠቁመናል? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ?
8. ጸሃፊው ሰላምታው እንዲደርስለት የሚጠይቀው ለማን ነው? ከሰላምታው አቀራረቡ ስንመለከት የቤተ ክርስትያኒቱን ምዕመናኑን በምን መልኩ ነው ከፍሎ የሚያያቸው?
9. በዚህ ዘመን ሰዎች ምዕመናንን ከፍለው የሚጠሩባቸውን ስያሜዎች ተናገር፡፡ ለምንድነው እንደነዚህ ዓይነት መጠሪያዎች አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉት? ተገልጋይ ብቻ ወይም ተራ የሆነ አማኝ ስለሌለ ይህንን ዓይነት መጠሪያ ላለመጠቀምና ሌሎችም ሲጠቀሙበት ስህተቱን ማሳሰብ ችላ አትበል፡፡